# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 142 ጥር 26 2003 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

በቱኒዚያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ እንደ ሰደድ እሳት ወደ አካባቢው አገሮች እየተዛመተ ነው። ወላፈኑ አልጄሪያ፣ ሞሮኮና ሊባኖስን አዳርሶ አልባኒያ ደርሷል። አሁን የእሳቱ ሰደድ ግብጽና የመን ውስጥ በመንቦግቦግ ላይ ይገኛል። ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ህዝብ ተባብሮ እንዲነሳ ይጠይቃል። ተመሳሳይ ሁኔታ በአገራችን ቢከሰት መከተል ስለሚኖርብን ስልቶች እንድንወያይና፤ በጋራም በግንባር ቀደምትነት እንድንቆም ያሳስባል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## አሳፋሪ ከሆኑት የአሜሪካን አጋሮች መካከል፤ አንዱዋ ኢትዮጵያ መሆንዋ ተገለጸ

ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በአለም ዙሪያ ከምታደርገው ዲፕሎማቲክ ግንኙነት ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ8 አገሮች ጋር ያላት ወዳጅነት እጅግ የሚያሳፍር እንደሆነ ፎሪን ፖሊሲ በመባል የሚታወቅ አንድ በአሜሪካን አገር የሚታተም መጽሄት ዘገበ። ከ 3 ቀን በፊት በፈረንጆች አቆጣጠር ጃንዋሪ 31 ለንባብ የበቃውን ይህንን ዘገባ ለህዝብ ይፋ ያደረገው ፎረን ፖሊሲ የሚል ድህረ ገጽ እንደገለጸው በጸረ ሽብርተኝነት ሥም የቡሽ አስተዳደር ከኢትዮጵያው ዘረኛ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ጋር የመሰረተቺው ወዳጅነት ለአሜሪካ እጅግ አሳፋሪ ከሆኑት አንዱ እንደሆነና ቡሽን የተኩት አዲሱ ፕሬዝደንት ኦባማም ቢሆኑ ግንኙነቱን አለዘቡት እንጂ አልቀየሩትም ሲል ተችቶአል። ፎሪን ፖሊሲ እንደ ኢትዮጵያ ሁሉ አሳፋሪ ናቸው ያላቸውን ሌሎች ሃገራትም የዘረዘረ ሲሆን እነዚህ ሃገራትም ሳውዲት አረብ፣ የመን፣ ዮርዳኖስ፣ ዩጋንዳ፣ አዝበኪስታን፣ ካዛኪስታንና ቬትናአም መሆናቸውን ገልጹአል።

ፎሪን ፖሊሲ አሳፋሪ ናቸው ያላቸውን አገራት መሪዎች ተግባራት በዝርዝር ያወጣ ሲሆን ሁሉም በየአገራቸው የዜጎቻቸውን ሰብአዊ መብት ከመጣስ ጀምሮ በሙስናና በሥልጣን ብልግና የሚታወቁ ናቸው ብሎአቸዋል። የመለስ ዜናዊን ተግባር በልዩ ሁኔታ የዘረዘረው ፎረን ፖሊሲ ባለፈው ግንቦት ወር 2002 በተካሄደው ምርጫ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ 99.6 በመቶ በሚሆን ውጤት አሸንፊያለሁ በማለት ማሳወቁን፣ ይህንም ተከትሎ በኢትዮጵያ የነበረው እጂግ ዝቅተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ጭራሹን መጥፋቱን እንዲሁም የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሃገሪቱ የፖለቲካ ስራን ለመስራት የሚችሉበትን ሁኔታ ጭራሹን እንደዘጋው ገልጹአል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ህንድ ከኢትዮጵያ ወደ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ ለም መሬት መውሰዱአ ታወቀ

ኢትዮጵያ ለህንድ በሊዝ ኪራይ የሰጠቺው ወደ ሁለት ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ ለም መሬት ህንድ የዜጎቹዋን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እያከናወነች ላለው ተግባር ትልቅ አስተዋጾ ይኖረዋል በማለት ኢኮኖሚክ ታይምስ በመባል የሚታወቅ ጋዜጣ ዘገበ::

ኢኮኖሚክ ታይምስ በመባል የሚታወቀው ጋዜጣ ባወጣው ጽሁፉ ኢትዮጵያ ለህንድ እስካሁን 1.8 ሚሊዮን ሄክታር ለም መሬት በሰባ ዓመታት የሊዝ ኪራይ ማስረከቡዋንና ይህም ለህንዳዊያን የምግብ ዋስትና መረጋገጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ገልጹአል:: ዘገባው ይህ ከኢትዮጵያ የተገኘ ድንግል የእርሻ መሬት ከፍተኛ የግብርና ሰብል አምራች የሆነቺውን የፑንጃብ ክፍለግዛት 50 በመቶ የሚሆነውን የቆዳ ሽፋን የሚሸፍን እንደሆነና ይህም ህንድ 25 ከመቶ የሆነውን የሩዝ ፍጆታዋን የምታገኝበት እንደሆነ ከዚህም የተነሳ የህንድ ባለስልጣናት ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማቸው ዘግቡአል::

የመረጃ ድረገጹ በህንድ አገር ጉብኝት እያደረገ ያለውን የኢትዮጵያ ግብርና ሚንስትር ተፈራ ደርበውን በመግለጽ እንደዘገበው የወያኔ አገዛዝ እስካሁን ድረስ ለህንድ ሃገር ቃል ከገባውና ካስረከበው የለም መሬት ሽያጭ በተጨማሪ ለውጭ ሃገራት ኢንቨስተሮች ለመሸጥ ካዘጋጀው ተጨማሪ 3.6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ የህንድ ኢንቨስተሮች የፈለጉትንን ያህል ቢወስዱት ወይንም ሙሉ በሙሉ ጠቅልለው ቢይዙት ደሳታቸው እንደሆነ መግለጹን አያይዞ ዘግቦአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የተሻሉና ለም በሆኑ ክልሎች የሚገኘውን ሰፋፊ የርሻ ቦታ በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን በማፈናቀል የመሬት ሽያጩን የጥድፊያ ዘመቻ በስፋት እንደቀጠለበት ስንዘግብ መቆየታችን አይዘነጋም:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ በግዳጅ ከቀያቸው እየተፈናቀሉ የሚገኙት አርሶ አደሮች ጥያቄ ሲያነሱ እስከ ሞት ድረስ የሚደርስ እንግልት እንደሚጠብቃቸው መግለጻችን ይታወሳል::

## በግብጽ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ እንደቀጠለ ነው፤ ሆሲኒ ሙባረክ በፕሬዘዳንትነ አልቀጥልም አሉ

ከቱኒዚያ ተነስቶ በርካታ ሃገራትን እየናጠ ያለው አመጽ ግብፅ ላይ ዛሬም እንደቀጠለ ሲሆን ሙባረክ ከትናንት6ይ7ኡይ በስቲያ ምሽት ለግብጻዊያን ባደረጉት ንግግር በፕሬዘዳንትነ አልቀጥልም ማለታቸው ታውቁአል ። ሙባረክ ለፕሬዘዳንት ይፈቀድ የነበረውን ገደብ የለሽ የስልጣን ዘመን ህገ እንዲሻሻል አደርጋለሁ ብለዋል:: ይሁን እንጂ የግብጽ ህዝባዊ አመጽ ተሳታፊዎች ሙባረክ አሁኑኑ ልቀቅ፣ አሁኑኑ ከሃገር ጥፋ በማለት ጩኸታቸውን እንደቀጠሉ ሲሆን ሙባረክ ያደረጉትን ንግግርም አለመቀበላቸውን እያሳወቁ ነው:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሙስሊም ወንድማማቾች በመባል የሚታወቀው ፓርቲ መሪዎች ሙባረክ ዛሬውኑ ስልጣናቸውን እንዲለቁ ይህን የማያደርጉ ከሆነ ደግሞ የመጨረሻ እድላቸው የሚሆነውን ሰላማዊ ሰልፍ

## ግዜ

የፊታችን አርብ ላይ እንደሚያካሂዱ ከአልጃዚራ ዜና አገልግሎት ጋር በተደረገ ቃለምልልስ ገልጻዋል:: የግብጽ መንግስት ህዝባዊ ተቃውሞውን ለማገድ የሰዓት እላፊ ቢያውጅም አዋጁን ያካበረው አልተገኘም፣ ይልቁንም አመጹ ተባብሶ ህዝባዊ አመጽ ባነሱትና የሙባረክ ደጋፊዎች ነን ባሉ መካከ ግጭቶች ተፈጥረዋል:: (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የቱንዢያው ህዝባዊ ማእበል ተከትሎ ህውሀትና ተለጣፊዎቹ አስቸኳዋይ ስብሰባ እንዳደረጉ ታወቀ

ከቱኒዚያ በመነሳት ወደ ግብጽ ቀጥሎም ወደ የመን እንደሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ የመጣው ህዝባዊ አመጽ ዘረኛውና አምባገነኑን መለስን ዜናዊንና በዙሪያው የተኮለኮሉትን ሆድ አደሮች ከፍተኛ ውጠረት ውስጥ እንደከተታቸው የግንቦት 7 ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ከላኩት ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል። እንደውስጥ አዋቂ ምንጮች ዘገባ በተቃውሞው የተደናገጡት የህውሃት ማእከላዊ ኮሚቴ አባላት የሌሎች ተለጣፊ ድርጂቶች መሪዎችን በማካተት ውጥረቱን ለማርገብ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለመምከር ባለፈው ሰኞ ጥር 23 ቀን ልዩ ሰባስበ አድርገው እንደነበር ታውቁዋል። የወያኔው አገዛዝ በሰሜን አፍሪካ እየተቀጣጠለ በመጣው ጸረ አምባገነን ሰላማዊ ተቃውሞ ከፍተኛ መደናገጥ ውስጥ የገባበት ዋናው ምክንያት በወያኔ መሪዎች አይን ለረጅም ጊዜ ያለተቀናቃኝ በሥልጣን ላይ የቆዩት የሰሜን አፍሪካና መካከለኛው ምስራቅ አምባገነኖቹ ለዘመናት ያደራጁት የደህንነትና የጸጥታ ሃይሎች የተነሳባቸውን የለውጥ ማዕበል መቋቋም ተስኖአቸው ከህዝቡ ጎን በመቆማቸው እንደሆነና ለአመታት ጠንካራ ሸሪኮቻቸው የነበሩት የምዕራብ አገራት መንግሥታት በቅጽበት ተለውጠው ለተቃውሞ ወደ ጎዳናና አደባባይ ከወጣው ህዝብ ጎን እንደሆኑ ያለምንም ማወላወል ተደጋጋሚ መግለጫ በማከታተል በማውጣታቸው ነው ተብሎአል።

አንደ መለስ ዜናዊ በጸረሽብርተኝነቱ ዘመቻ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝደንት ጆርጅ ቡሽ ዋና ሸሪክ የነበሩት እና በ23 አመት የሥልጣን ዘመናቸው በአገራቸው ውስጥ ልማትንና ዕድገትን አስመዝግበዋል ተብለው በምዕራቡ አለም ሲወደሱ የነበሩት የቱንዚያው መሪ ቤነ አሊ፤ ህዝባዊ አመጽ ሲነሳባቸውና የአፈና መዋቅር ሆኖ ሲያገለግላቸው የነበረው ወታደርና ፖሊሲ ፊቱን ሲያዞርባቸው በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ መጠጊያ እንኳን ማግኘት አለመቻላቸው ለመለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ ላይ ሊፈጥር የሚችለው ድንጋጤ መገመት ከባድ እንዳልሆነ የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው።

በሰሞኑ የሰሜን አፍሪካ ሁኔታ የተደናገጡት የወያኔ ባለሥልጣኖችና የቅርብ አጋሮቻቸው በአገራችን ሊነሳ ይችላል ብለው የፈሩትን ህዝባዊ ተቃውሞ አስቀድሞ ለመምታት በህዝቡ ላይ የሥነልቦና ዘመቻ መክፈታቸውን ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ በላከው ዜና ገልጾአል። በአድስ አበባ ነዋሪ የሆኑትን (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጎጠኛው የወያኔ ቡድን ዘረፋውን አጡዋጡፎታል፤ መሬት ችብቸባ ተጠናክሮ መቀጥሉ ታወቀ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ ቡድን ቁንጮዎች በግብር በመዋጮና ኑሮን በማስወደድ ከህዝብ ከፍተኛ ገንዘብ ሲዘርፉና በውጭ አገርም በሚገኙ ባንኮቻቸው ሲያከማቹ የቆዩ መሆናቸው የሚታወቅ ሲሆን ይህ አልበቃ ብሉአቸው ደሀውን ገበሬ ከመሬቱ በማፈናቀል ከፍተኛ ዶላር ለሚከፍሉዋቸው አምባገነን መሪዎችና ድርጅቶች መቸብቸባቸውን አጡዋጡፈው እንደቀጠሉ መሆኑን ዊኪ ሊክስ ባወጣው ሚስጢራዊ መረጃ አጋለጠ።

እንደመረጃው ከሆነ የቀድሞው የናይጄሪያ መሪ ኦሌሴንጎ ኦባሳንጆ እና የጅቡቲው መሪ እስማኤ ኡማር ጉሌህ ከአዲስ አበባ ውጭ ከፍተኛ መጠን ያለው መሬት በረዥም ሊዝ ለሆቴል ግንባታ በሚል ስም መውሰዳቸው ሲታወቅ ኡማር ጉሌህ ከዚህ ቀደምም 7400 ሄክታር መሬት በመውሰድና ስንዴ በማምረት ወደ ጅቡቲ መላክ መጀመሩን አጋልጦአል። አንድ በግብጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር የሚመራ ቡድንም ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ከፍተኘ ስፋት ያለው መሬት ለመግዛት ድርድር የደረጉ ሲሆን አግሪ ቪይ በመባል የሚታወቀው የደቡብ አፍሪካ ኢንቨስትመንት ድርጅት 3.5 የአሜሪካ ዶላር በመመደብ የፍራፍሬ ማማምረትና ጭማቂዎችን በማዘጋጀት ወደ አውሮፓ ሀገራት ገበያ ለመላክ መዘጋጀቱም ታውቆአል፡፡ ሰሞኑን ደግሞ ቻድህ የሚባለው የህንድ ኩባንያ የአዲስ አበባን ሁለት እጥፍ የሚሆን መሬት እንዲሰጠው ጥያቀ ያቀረበ ሲሆን እስካሁን 22 ሺህ ሄክታር መሬት የተሰጠው ሲሆን በቀጣይነትም የጠየቀው ከ100ሺህ ሄክታር በላይ መሬት እንደሚሰጠው ቃል እንደተገባለት ለማወቅ ተችሎአል፡፤

ከዚህ ሁሉ መሬት የሚፈናቀለው ገበሬ ከብት እንኩዋን የማይገዛለት ገንዘብ እየተወረወለትና ከቦታው በግድ እየተፈናቀለ በገዛ አገሩ በየከተማዎቹ በስደት እንደሚሰቃይ የሚታወቅ ሲሆን በአካባቢው የቀረው ገበሬ ደግሞ በገዛ መሬቱ ላይ ለለት ጉርስ እንኩዋን በማትበቃ ገንዘብ እንዲያገለግልና ጉልበቱ እንዲበዘበዝ እየተደረገ መሆኑን በተለያየ ጊዜ መግለጻችን ይታወሳል።

ይህ ሁላችንንም በገዛ አገራችን ላይ የበይ ተመልካች ያደረገን መሆኑን የተናገሩ ሪፖርተራችን ያናገራቸው አንድ በአዲስ አበባ በጎዳና ላይ የሚኖሮ ተፈናቃይ ገበሬ በጣሊያንም ጊዜ እንዲህ አይነት ግፍ ያልደረሰ መሆንን አስታውሰው ከቤቴ ተፈናቅየ የሰው እጅ እያየሁ የምኖርበት ዘመን ላይ ከምደርስ ያኔውኑ በመልካሙ ጊዘ ሞቼ ቢሆን ይሻለኝ ነበር በማለት ሲቃ እየተናነቃቸው እንደነገሩት አስታውቆናል።

## ወጣት፤ የነብር ጣት!

ወጣት በነብር ጣት መመሰል ያንሰው እንደሆን እንጂ አይበዛበትም። የኢትዮጵያም ወጣት የነብር ጣት ሆኖ ያውቃል። አገራችን በጣልያን ፋሽስቶች በተወረረችበት ወቅት የጠላት ግዙፍ ኃይልና ፕሮፖጋንዳ ሳይበግራቸው፤ በአይሮፕላን የመጣን ወራሪ በውጅግራና ምንሽር ለማባረር ቆርጠው የተነሱ፤ የወቅቱን የአውሮፓ ኃያል መንግሥት ሠራዊትን በአበርኝነት ተፋልመው ነፃነታችንን ያስመለሱ ጀግኖቻችን በእድሜ ገና ለጋ ወጣቶች የነበሩ ናቸው። ከ1950ዎቹ ጀምሮ የተደረጉ ህዝባዊ ንቅናቄዎች በሙሉ የተጠነሰሱትና የተመሩት እድሜያቸው ከሠላሳ ዓመት በታች በሆኑ ወጣቶች ነው። በቅርቡም የ1997 ምርጫ ታሪካዊ እንዲሆን ያደረጉ፤ የሚያዝያ 30 ቀን 1997ን ታላቅ ሰልፍ ያደራጁ፤ ህዝብን አደፋፍረው ለምርጫ በማሰለፍ ግንቦት 7 ቀን 1997 ታሪካዊ እለት እንድትሆን ያደረጉ፤ በኋላም ድምፃችንን አናስነጥቅም በማለት የአግዓዚ ፋሽስቶችን በድንጋይና ዱላ የገጠሙ ወጣቶች ናቸው። በእነዚህ ሁሉ ትግሎች ወጣቶች በግንባር ቀደም ተፋላሚነትና በመሪነት ተሳትፈዋል። ሽብሬ ደሳለኝን ጨምሮ በርካታ ወጣቶች ህይወታቸውን ሰውተዋል፤ ከዚያ በቁጥር በጣም የበዙት ደግሞ አካሎቻቸውን አጥተዋል። የኢትዮጵያ ወጣት በእርግጥም የነብር ጣት ሆኖ ያውቃል።

የወጣቱን ቁልፍ ሚና ጠንቅቆ ስለሚያውቅም ነው በመለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ወጣቱን በማሽመድመድ ሥራ ላይ ያተኮረው። ይህ ፋሺስታዊ ቡድን በወጣትነቱ "መብት ተነፈግሁ" ብሎ ብረት እንዳላነሳ ሁሉ የዛሬው ወጣት ስለመብቶቹ አንዳች ቃል እንዲተነፍስ አይፈቅድም። ጉጅሌው ባደረሰበት ተደጋጋሚ የግፍ ጥቃት ሳቢያ የዛሬው ወጣት ኑሮው የተጎሳቆለ፤ የነገ ተስፋውም የጨለመ እንዲሆን አድርጎታል።

መለስና እኩይ ቡድኑ የኢትዮጵያን ሃብትም ተከፋለው ስለጨረሱት ለወጣቱ የተረፈው እዳ ብቻ ሆኗል። ለም መሬታችን ለባዕዳን በመሸጡ የገጠሩ ወጣት የሚያርሰው ቁራሽ መሬት እያጣ መሰደድ ከጀመረ ውሎ አድሯል። ወጣት ገበሬ ደቡብ አፍሪካ ድረስ ለመሰደድ ከቀዬው ነቅሎ የተነሳው በመለስ የአገዛዝ ዘመን ብቻ ነው። በገጠርም በከተማም የሚገኙ ወጣት ሴቶች ወደ አረብ አገራት ለመሄድ በረሃ ማቋረጥ፤ ባህርን በታንኳ መሻገር የጀመሩት በዚሁ የግፍ አገዛዝ ዘመን ነው። ዘመናዊ ትምህርት ያገኘው ወጣትም በተማረው ትምህርት አገሩንና ወገኑን የማገልገል ህልሙ ተጨናግፎ ስደት እጣ ፈንታው የሆነው በመለስ የአገዛዝ ዘመን ነው።

ኢትዮጵያዊ ወጣት ክብሩንና ነፃነቱን ለገንዘብና ለተሻለ የሥራና የትምህርት እድል ሲል አሳልፎ እንዲሰጥ ሲደለል ቆይቷል። በዚህም ምክንያት አንዳንዱ ወጣት የማያምንበት እየሰበከ፤ ከህሊናው ጋር ተጣልቶ የወያኔ ሎሌ ሆኖ እንዲኖር ተፈርዶበታል። በጫትና ሌሎችም ሱሶች አዕምሮው የደነዘዘው ወጣት ቁጥርም አስደንጋጭ ነው።

ከዚህ ሁሉ የከፋው ደግሞ ወጣቱን በዘር በማደራጀት እርስ በርሱ እንዲጣላ መደረጉ ነው። በየጊዜው በሚፈለፈሉ "የወጣቶች ፎረሞች" አማካይነት የወጣቱ ወኔ ተሰልቦ አድርባይነትን እንዲለማመድ ተደርጓል። የሊባስ ወጣቶች ለግብፃዊያን የእድሜ እኩዮቻቸው የድጋፍ ሰልፍ ሲወጡ እኛ አገር ግን የጎንደሩ ለባሌ፤ የሸዋው ለአሩሲ፤ የትግራዩ ለባህርዳር የሃረሩ ለጅጅጋው ባዕድ እንዲሆን፤ በጥርጣሬም እንዲጠባበቅ፤በሰበብ አስባቡም እንዲቆራቆስ ተደርጓል። ወያኔ ወጣቶችን በወጣቶች ላይ የሚያዘምት እርኩስ ኃይል ነው።

መለስ ለትልቁም ለትንሹም ጉዳይ "ጣት እንቆርጣለን" ብሎ የሚዝተው አለነገር አይደለም። እሱና ጉጅሌው የኢትዮጵያን ህዝብ ሥልጣን ከነጠቁ ወዲህ የኢትዮጵያ ጣት የሆነውን ወጣትን ነጥለው ለመቁረጥ እየገዘገዙ ናቸው። ለዚህ ጥቃት ምላሻችን ምንድነው? ከጎረቤቶቻችንስ ምን እንማራለን?

መለስ ዜናዊ በኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ላይ እንዳደረገው የከፋ ባይሆንም የቱኒዝያው ፕሬዚዳንት ቤን ዓሊ በቱኒዝያ ወጣቶች ህይወት ተጫውቷል። ቱኒዝያ ግን እድለኛ ነች። መሃመድ ቦዛዚና ሁሴን ያሲን ፈልዲን የመሰሉ ልጆችን ወልዳለችና ዛሬ አምባገነኑን ከጫንቃዋ አውርዳ ጥላለች። መሃመድ ቦዛዚ የሃያ አራት ዓመት የዩኒቨርስቲ ምሩቅ ቢሆንም ቋሚ ሥራ ስላለነበረው አትክልትና ፍራፍሬ እየሸጠ ይተዳደር ነበር። የቤል ዓሊ ፓሊሶች በተደጋጋሚ እቃውን ዘረፉት፣ ሰደቡት፣ ደበደቡት። መሃመድ ለራሱ ክብር የሚሰጥ ወጣት በመሆኑ አንባገነኑ መንግሥት የጫነበትን ውርደት መቀበል አልፈለገም። ወጣቱ መሃመድ ነፃነቱን ከሚያጣ ህይወቱን ማጣት መረጠ። እከተማው ማዘጋጃ ቤት በራፍ በገዛ ራሱ ላይ እሳት ለኮሰ፤ ከሁለት ቀናት በኋላም ህይወቱ አረፈች። ሁሴን ናዲ ፈልሂም የሃያ ስድስት ዓመት ወጣት ነበር። እሱም በቢን ዓሊ አገዛዝ መዋረድ በቃኝ ብሎ 30 000 ሜጋ ዋት የሚያሰራጭ የኤሌክትሪክ ሽቦ ጨብጦ ተሰዋ። የሁለቱ ወጣቶች መስዋዕትነት ከቱኒዝያ አልፎ አፍሪቃና መካከለኛውን ምሥራቅ አነቃ። መሃመድና ሁሴን የቱኒዝያ ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪቃ የነብር ጣቶች ናቸው።

በየትም አገር ቢሆን የወጣቱ የወደፊት እድል ያለው በራሱ በወጣቱ እጅ ውስጥ ነው። የግብፅ ወጣቶች ለሠላሳ ዓመታት አጎነበሱ። ሙባረክ በተደጋጋሚ "በከፍተኛ ድምፅ" እየተመረጠ ፎለለባቸው፤ ተዝናናባቸው። መለስ በወጣቶች ፎረም እንደሚያደርገው ሁሉ ሙባረክም ወጣቶችን እየሰበሰበ ስለ ዲሞክራሲ "አስተምሯቸዋል"። ትዕቢትና ግፍ በዝቶባቸው በተነሱ ጊዜ ግን በስምንት ቀናት አመጽ አንበረከኩት። አሁን ግብፅ ውስጥ ጨዋታው ተቀይሯል። አጥቂው ተከላካይ፤ ተከላካዩ ደግሞ አጥቂ ሆኗል። ሙባረክ "የስምንት ወር ጊዜ ስጡኝ" ብሎ "አንሰማህም" ብለውታል።

ሠላሳ ዓመታት ሲያጉረመርሙ የቆዩ ግብፃዊያን እና ሃያ ሶስት ዓመታት ሲታሹ የቆዩ ቱኒዚያዊያን እናቶችና አባቶች በወጣቶቻቸው ግንባር ቀደም ተጋድሎ ዛሬ አፋቸውን ሞልተው ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ወጣት ከግብፅና ከቱኒዝያ ወጣት በምን ያንሳል?

## በግብጽ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በግብጽ በተነሳው አመጽ እስካሁን ድረስ በይፋ ሪፖርት የተደረገ ከ 150 የሚበልጡ ሰዎችን ህይወት አጥፍቷል የሙስሊሞቹ ወንድማማችነት በመባል የሚታወቀው የተቃዋሚ ቡድን ሆሲኒ ሙባረክ እስካሁን የወሰዱዋቸውን ርምጃዎች አልተቀበለውም። ቡድኑ ከትናንት በስቲያ ጠርቶት በነበረው ግዙፍ ትዕይንተ ህዝብ የውጭ መገናኛ ብዙኃን እንደሚሉት በተለይ በመዲናይቱ ካይሮ በታህሪር አደባባይ የተሰበሰበው ወደ ሁለት ሚልዮን የሚሆን ህዝብ ፕሬዚደንት ሙባራክ ስልጣናቸውን አሁኑኑ ይልቀቁ በማለት በጭኸት ሲያናውጠው ውሉአል።

በሌላ በኩል ደግሞ አልጃዚራ በትናንትናው እለት ባስተላለፈው ዘገባ በግብጽ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ አመጽ ተከትሎ በሱዳንም ወጣት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ባለፈው እሁድ ማካሄዳቸውን ነገር ግን የሱዳን ወታደሮች በሰልፈኞቹ ላይ ከፍተኛ ድብደባና እስራት መፈጸማቸውን ከድብደባ ጋር በተያያዘም አንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ የሆነ ወጣት መገደሉን ገልጹአል:: አልጃዚራ የሱዳን ፖሊሶች ወደ እስር ቤት ካጎሩአቸው የሱዳን ዜጎች ውስጥ ጋዜጠኞች እንደሚገኙበትም አክሎ ገልጹአል::

ከሁለት ሳምንታት በፊት በቱኒዚያ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ በርካታ ሃገሮች ላይ ህዝባዊ አመጾች እንዲነሱ ምክንያት እንደሆነ እየተነገረ ባለበት በዚህ ወቅት የየመኑ ፕሬዘዳንት አሊ አቡላሂ ሳለህ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አሁን የያዙት የስልጣን ዘመናቸው ከተጠናቀቀ በሁአላ ከስልጣን እንደሚወርዱ ለህዝባቸው ቃል ገብተዋል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ የዮርዳኖሱ ንጉስ አብደላ በሃገራቸው የተነሳውን ህዝባዊ አመጽ ተከትሎ መንግስታቸውን ያፈረሱ ሲሆን በምትኩ አዲስ ካቤኔ በማቋዋቋዋም ላይ መሆናቸው ታውቁአል:: ይሁን እንጂ የዮርዳኖስ ህዝብ የተወሰደው ርምጃ በቂ አይደለም በማለት አመጹን እንደቀጠለ ይገኛል::

በሰሜን አፍሪቃ የተቀጣጠለው ህዝባዊ አመጽ የበርካታ ሃገራት አምባገነን መንግስቶችን እያርበደበደ ሲሆን ከሰሜን አፍሪቃም ዘሎ የአሜሪካ አጋር እንደሆነች የምትታወቀው ፕልስታኒያ መንግስት ባስቸኩአይ አዳዲስ የመንግስት ባለስልጣናት የመምረጥ ስራ እንደሚያከናውን እየገለጸና ህዝቡንም እየተለማመጠ እንደሚገኝ የዜና አውታሮች ገልጸዋል::

ይሄው የዓመጽ ማእበል ከሰሜን አፍሪቃ አልፎ መካከለኛውንና ምስራቅ አፍሪቃንም እያነቃነቀ እንደሚገኝ በርካታ የመገናኛ ብዙሃን እየገለጹ ሲሆን በተለይም የወያኔው አምባገነን አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝባዊ አመጽ ይነሳል በሚል ፍርሃት ተውጦ የሚይዝ የሚጨብጠውን በማጣቱ ከወዲሁ አሳፋሪ የሆኑ ርምጃዎችን መውሰድ መጀመሩ እየተዘገበ ይገኛል:: አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በሃገሪቱ ውስጥ ተቆጣጥሮ እንደፈለገ በሚያዝባቸው የዜና ማሰራጫዎቹ በአሁኑ ሰአት በአፍሪቃ እየተካሄደ ያለውን የህዝብ አመጽ ካለመዘገቡም በላይ በኢትዮጵያ የሚገኙ ዜጎችን በስደት የሚገኙ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሃገር ለማጥፋት እየሰሩ ስለሆነ፣ ተጠንቀቁ፣ ልጆቻችሁንም ባይነ ቁራኛ ተከታተሉ እያለ እንደሚገኝ ታውቁአል::

አምባገነኑና ዘረኛው የወያኔ ቡድን እጅግ በርካታ የሚባሉ ችግሮች እንዳሉበት ኢትዮጵያዊያንም የሰቆቃ ኑሮ እየገፉ እንደሆነ በስፋት ሲዘገብ ቆይቱዋል:: አምባገነኑ ዘረኛ አገዛዝ በርካታ የሆኑ መገናኛ ብዙሃንን እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያዊያን እንዳይከታተሉ ሌት ከቀን እየሰራ ቢገኝም ሁኔታዎች ሁሉ ከቁጥጥር በላይ እንደኑበትና ኢትዮጵያዊያንም ከውያኔ የዜና ማሰራጫዎች ይልቅ ሌሎችን አማራጭ የዜና አውታሮች እየተከታተሉ እንደሆነም ታውቁአል:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዘጋቢያችን ካዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ በሃገኢቱ የኢንተርኔት አገልግሎት ማቋዋረጥ:: በአዲስ አበባ ከተማ በመዘዋወር ዘጋቢያችን ያናገራቸው ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ ወጣቶች እሳተ ገሞራው መፈንዳቱ አይቀሬ ነው፣ በዚህ የሚጠራጠር ካለ በጊዜ ሂደት የሚታይ ጉዳይ ነውና ይህን ጊዜ በትግስት ይጠብቅ ብለዋል::

## አሳፋሪ ከሆኑት የአሜሪካን አጋሮች መካከል

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ፎሪን ፖሊሲ በኢትዮጵያ እጂግ በርካታ ንጹሃን ዜጎች እንዲሁም በርካታ የተቃዋሚ ፓለቲካ ፓርቲ አባላት ያለበቂ ምክንያት እየታፈሱ ወደ እስር ቤት እንደሚወሰዱ እንዲሁም በእስረኞች ላይ የወያኔው አገዛዝ እያደረሰ ያለውን እስራትና በደል በዝርዝር አስቀምጡአል፣፣ ከዚህም በተጨማሪ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቁአማት ላይ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ የወሰዳቸውን ተገቢ ያልሆኑ ርምጃዎችን፣ በነጻ ሚዲያ ተቁአማትና ጋዜጠኞች ላይ እየተወሰዱ ያሉ አፋኝ ርምጃዎችን በሙሉ በዝርዝር አስቀምጡአል:: ፎሪን ፖሊሲ በዚህም ምክንያት በአሜሪካን ሃገር የሚገኘው ፍሪደም ሃውስ ኢትዮጵያን ቀደም ብሎ በከፊል ነጻ የሆነች እያለ ይጠራበት ከነበረው ደረጃ ከአፈና ፍጹም ነጻ ያልሆነች ሃገር ወደሚለው ደረጃ እንድትወርድ ማድረጉን ጠቁሙአል::

በዘገባው አሜሪካ በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን አፈና በግልጽ የምታውቅ በመሆንዋ የወያኔው አገዛዝ በሰባዊ መብቶች ላይ የሚያካሂደው አፈና ተገቢ እንዳልሆነ ወቀሳ እየሰነዘረች እንደሆነ ቢታወቅም፣ ለሰብአዊ ርዳታ በማለት የምትልከው ገንዘብ ለፖለቲካ ፍጆታ እየዋለ እንደሆነ መረጃው እንዳላት ቢታወቅም በየዓመቱ ወደ ስድስት መቶ ሚሊዮን የአሜሪካን ኣላር ማለትም ወደ አስር ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር የሚጠጋ ገንዘብ አሁንም መለገስ መቀጠሉዋ የሚያሳፍር ነው ብሉዋል::



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## ለስኬታማ ህዝባዊ አመጽ ልንጠቀምባቸው የሚገቡን ዘዴዎች

የሰሜን አፍሪካ እና የመካከለኛው ምስራቅ ወጣቶች፥ "አገሮቻችን ከዚህ የተሻሉ ናቸው፤ ያለንበት ችጋር፣ ጭቆና እና ውርደት መገለጫችን ሆኖ ሊቀር አይገባውም። እንዲህ ባለ ኋላ ቀርነት ውስጥ እራሳችንን ልናይ አልቻልንም። የተቀረው አለም ህዝብ እርቆ ሄዷል፤ እኛ ምን አንሶብን?" በሚል ጥያቄ፤ ንዴት እና ቁራጥነት ተነሳስተው የነጻነትን እሳት አቀጣጥለዋል።

ቱኒዚያውያን ከአንድ ወራት በፊት ለሃያ ሶስት አመታት የገዛቸውን አምባገነን ካስፈረጠጡት በኋላ፣ የነጻነት መንፈስ እሳት በግብጽ ላይ ወርዶ ለአስርተ አመታት የቆየን ፍርሃት በልቶታል። ቀድሞ አንገታቸውን ዝቅ ያደረጉ ቀና ብለዋል። ትናንት ፖሊስ ጌታ ነው ብለው ያመኑ ድሃ አደጎች የትልቅነትን መንፈስ ተላብሰዋል። የሰለሉ እጆች ጠንክረዋል። የተሰበሩ መንፈሶች ተገጣጥመዋል። የፈረሱ ግንቦች ተጠግነዋል። የጠወለጉት አበቦች ለምልመዋል። ጨለማን ያዩ የነበሩ በተስፋ ተሞልተዋል። ትናንት ሲረገጡ እራሳቸውን ዝቅ አድርገው የተቀበሉ፤ ዛሬ በቀጥቃጦቻቸው ትክክል ቆመው እውነትን በድፍረት የሚናገሩ ሆነዋል።

ለሰላሳ አመታት በአንድ ገዢ በትር ስር የኖሩት ልጆች፣ የነጻነት ጸሃይ ከአድማስ ባሻገር ተደብቃ እንዳትቀር በጩኸታቸው አስገድደዋታል...እሷም ብቅ የምትል ትመስላለች።

ህዝባዊው ሞገድ ግብጽ አላቆመም። የመንም እየተናወጠች ነው። አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ዮርዳኖስ፣ እና ጎረቤታችን ሱዳንም እጣ ደርሷቸዋል። በሳውድ አረቢያ እና በጋቦንም መለስተኛ የተቃውሞ ሰልፎች ተስተውለዋል። የአልጄሪያ እና የሶሪያ የዴሞክራሲ ታጋዮች በሚቀጥለው ወር የተሟሟቀ ተቃውሞ ለማካሄድ በዝግጅት ላይ እንደሚገኙም ተሰምቷል።

እንግዲህ ከዚህ ሁሉ በስተጀርባ፤ በተለይም ከስኬታማው የቱኒዚያ ንቅናቄ እና ግብጽን እያንቀጠቀጠ ካለው እንቅስቃሴ በስተጀርባ፤ የሚያስገርሙ የወጣቶች የፈጠራ ሃሳቦች እና ድርጅቶች ተስተውለዋል። ለረዥም አመታት፥ በርካቶች በነዚህ አገራት እንዲህ ያለ ህዝባዊ አመጽ መንግስት ሊጥል አይችልም፤ የመንግስታቱ አፈና ከባድ ነው ብለው ሲያጣጥሉ ቆይተዋል። ያም ደግሞ በተወሰነ ደረጃ እውነት ነው፤ ህዝቡ እነዚህን ሰልፎች ለማካሄድ ብዙ መስዋእትነት እየከፈለ ነው። ብዙ የፖለቲካ ተንታኞች፥ ይህ የሚካሄደው በአገራችን ቢሆን ኖሮ ከዚህ እጅጉን የከፋ እና በብዙ እጥፍ ያየለ መስዋእትነት እንደሚከፈል ይናገራሉ።

ይሁን እንጂ፥ በነዚህ በሰሜን አፍሪካ አገራት ከተከሰቱ ህዝባዊ አመጾች የምንማረው አንድ ቁምነገር አለ። ይህም ቁምነገር ለአገራችን ወጣቶችም ቢሆን አስተማሪ ነው። በአጭሩ ሲቀመጥ፥ "ለሁሉ ችግር መፍትሄ ያለው በገዛ እጃችን ውስጥ ነው።" የሚለው ነው። በአሁኑ ሰዓት፥ በኢትዮጵያ ውስጥ የአመጽ ሰልፍ የጠራ ቡድን የለም። ይሁን እንጂ፥ በሰሞኑ ክስተቶች በመገፋፋት፣ ብዙ ወጣቶች ተነሳሽነት እያሳዩ ይገኛሉ።

ስለዚህም የቱኒዚያ እና የግብጽ ወጣቶች፥ ከነፍሰ ገዳይ የመንግስት የደህንነት ሃይሎች እና ፖሊሶች ለማምለጥ እና ስኬታማ አመጽ ለማካሄድ ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች ውስጥ የተወሰኑትን፤ እንዲሁም ሌላ ቦታ የተገኙ ሃሳቦችን ሰብስበን ለማካፈል ወደናል። እንደሚከተለው እናቀርባቸዋለን።

1. በቱኒዚያ እና በግብጽ ህዝባዊው አመጽ ያለ ከልካይ እንደ ጎርፍ እንዲፈስ ከረዱት ዘዴዎች አንዱ፥ ሰልፈኞቹ በፖሊስ ላይ ያሳዩት ብልጣብልጥነት/ወይም ወጣቶቻችን እንደሚሉት ሸወዳ ነው። የፖሊስ መኪና ሊገባባቸው በማይችሉ ትናንሽ የመንደር መንገዶች ላይ በየሰፈሩ መሰብሰብ እና ሰልፉን እና የአብሮነትን ስሜት ማሟሟቅ፤ የፖሊስ ወይም የደህንነት ሰራተኞች ቁጥር ከህዝብ ቁጥር ጋር ሲነጻጸር ሁልጊዜም ቢሆን ዝቅተኛ መሆኑን መረዳት፤ በተጨማሪም፥ ፖሊሶች ብቻቸውን ወዲያ ወዲህ ለማለት ስለሚፈሩ በቡድን መጓዛቸው ሽፋናቸውን እንደሚቀንስባቸው ማወቅ፤ እና የመሳሰሉት ተስተውለዋል።
2. በቱኒዚያ፥ ሰልፎች የጀመሩት በትናንሽ ከተሞች ነው። ከዛ ቀስ እያሉ ወደ ዋና ከተማው መጡ። ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ፥ የአዲስ አበባ ህዝብ ብቻውን የተጨፈጨፈው ተቃውሞ የተጀመረው እዛ ስለሆነ እና አብዛኛው ፌዴራል ፖሊስ እና በአስር ሺሆች የሚቆጠሩ የጦሩ አባላት በመዲናይቱ ስለተሰባሰቡ ነው። ተቃውሞ የሚጀመረው በሺሆች በሚቆጠሩት የኢትዮጵያ መንደሮች ቢሆን ግን፥ አገዛዙ ያንን ለመቆጣጠር ሲል ፖሊሶቹን ወደየክፍላተ አገራቱ ይልካል። ያም ሃይሉን ይለጥጥበትና ይዳከማል። አዲስ አበባ ላይ ሃይሉ ከተዳከመ ደግሞ፥ በሚሊዮኖች የሚቆጠረው የከተማይቱ ህዝብ የተቀሩትን የፖሊስ እና የደህንነት ሰራተኞች ተቋቁሞ የአራት ኪሎን ቤተመንግስት እንደ ንብ የማይወርበት እና አምባገነኑን በቁጥጥር ስር የማያውልበት ምንም ምክንያት አይኖርም። አገዛዙ ይህንን ፈርቶ በገጠር የሚከሰቱ ተቃውሞዎችን ለመቆጣጠር የጦር ወይም የፌዴራል ፖሊስ ሃይሎችን ካልላከ ደግሞ፣ ያም ይጎዳዋል። ምክንያቱም፥ እያንዳንዱ የገጠር ነዋሪ እየተነሳ የወያኔ ካድሬዎችን፣ ሰላዮችን እና ሚሊሻዎችን በቁጥጥር ስር ሲያውል፤ ቀጥሎ ያለው መንደርም የልብ ልብ እያገኘ ያንኑ ያደርጋል፤ ያም እየተስፋፋ ይሄድና የአገዛዙን ውድቀት ያፋጥነዋል።
3. ፖሊስን ማዳከም። ሰሞኑን በግብጽ፥ ወጣቶቹ ከፖሊስ ጋር የድመት እና የአይጥ ጫወታ ሲጫወቱ ነበር ይባላል። አንድ የፖሊሶች ቡድን መጥቶ አንድ የወጣቶች ስብስብ በስንት መከራ ሰብሮ እና ወጣቶቹን በተለያየ አቅጣጫ አሯሩጦ እፎይ ከማለቱ፤ በአስር አቅጣጫ የሮጡት ልጆች መንደራቸውን ከማንም በላይ ስለሚያውቁ እንደገና አንድ ቦታ ተሰብስበው ቁጭ ይላሉ። ፖሊስን የማዳከም ጥቅም እራሱን የሚገልጠው ህዝባዊ አመጹ ለቀናት ሲቀጥል ነው። የተዳከመ ፖሊስ ህዝቡን መጋፈጥ ይሳነውና ሰልፉ ከቁጥጥሩ ውጪ ይሆናል፤ የስፋም ይቆርጣል።
4. የፈረቃ ሰልፍ። የግብጽ የሰልፍ አቀናባሪዎች፤ ህዝቡ በፈረቃ ሰልፍ እንዲወጣ መልክት አስተላለፉ። ማለትም፥ የመጀመሪያው ፈረቃ ለስምንት ሰአታት ሲሰለፍ፣ ሁለተኛው ለቀጣኡ ስምንት ሰዓታት፤ የተቀረው ደግሞ ለቀጣዩ። ህዝቡ ብዙ ሚሊዮን ከመሆኑ የተነሳ፣ እንደዚህ እየተፈራረቀ ሌሊቱን ሙሉ መንገድ ላይ ለመቅረት ይችላል። ፖሊሶች ግን በቁጥር ትንሽ ስለሆኑ፣ እንደዚህ በፈረቃ እንስራ ቢሉ ቁጥራቸው የባሰውኑ ያንሳል። ይህ ፖሊሶቹን ከማዳከሙ በተጨማሪ፤ ሌሊት ላይ በየቤቱ በመዞር የአመጹ መሪዎች ናቸው ብለው የሚጠረጥሯቸውን ዜጎች ለማሰር የሚያስፈልጋቸውን ፋታ አይሰጣቸውም።
5. የታቀደ መበታተን እና ፖሊስን አሳስቶ ህዝቡ ወደሚፈልገው አቅጣጫ መምራት። በአንድ ወቅት በመራቤቴ አካባቢ፣ ህዝብ አምጿል የሚል ወሬ ተሰምቶ፣ ያንን በቁጥጥር ስር ለማዋል ወደ ከተማዋ የተላኩትን የደህንነት ሰራተኞች፣ ህዝቡ "ሽፍታ! ሽፍታ!" ብሎ እየጮኸ ወደ ጫካ መራቸው ይባላል። እዛ ምን እንደተደረጉ አይታወቅም። ነገር ግን ተመልሰው አልመጡም። ለማንኛውም፥ በተለያየ አቅጣጫ በመበተን እና ፖሊሶች ተከትለው እንዲመጡ በማድረግ፤ ህዝብ የቁጥር አብላጫ ያለው መስሎ ከተሰማው፤ በቁጥጥር ስር ሊያውላቸው ይችላል። ይህኛው ዘዴ፥ ፖሊስ እና ደህንነት ከማዳከም አኳያም ትልቅ ጥቅም አለው።
6. ብቁ የሆነ የመረጃ መለዋወጫ እና ለህዝብ መልክት ማስተላለፊያ ማግኘቱም ለሰልፎቹ ስኬት ቁልፍ ነበር። ቱኒዚያ እና ግብጽ ከአገራችን ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ የሆነ የኢንተርነት አገልግሎት ሽፋን ያለባቸው አገራት በመሆናቸው ወጣቶች ለመገናኘት እና ሃሳብ ለመለዋወጥ ችግር አልነበረባቸውም። ይሁን እንጂ፥ መንግስታቶቻቸው አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ ያም ተዘጋባቸው። ያ ግን ተቃውሟቸውን አላቆመውም። በሁለቱም አገራት፥ ደርግን የሚቃወሙ ወጣቶች በአገራችን ያደርጉ እንደነበረው፣ ወጣቶች በየግድግዳው ላይ መፈክሮችን በመጻፍ ህዝባቸውን ያበረታቱ እና አምባገነኖቹን ይቃወሙ ነበር።
7. ሰሞኑን ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ፌስቡክ በተባለው የኢንተርነት መገናኛ መረብ ላይ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሲካፈሉት አየሁ ብለው አንድ አድማጫችን የላኩልን ዘዴ ደግሞ በብር ላይ ተቃውሞን መጻፍ ነው። ይህ ሃሳብ ከዚህ ቀደም በሌሎች አገራት በስራ ላይ የዋለ ሲሆን፤ ብር እራሱን በራሱ ስለሚያጓጉዝ መልክቶች በፍጥነት እንዲዘዋወሩ ይረዳል።
8. መልክቶችን የአገዛዙ ሰላዮች ሳያዩ ማዘዋወር በትኩረት ቢታሰብበት ከማንም በላይ ለኢትዮጵያውያን ይቀላል። ከጥቂት አስርተ አመታት በፊት አደን ማደን በህግ ክልክል ነው የተባሉ አባቶቻችን፤ ባጠመዱት ወጥመድ ሲሮጥ መጥቶ የገባላቸውን ድኩላ ደብቀው ወደቤት ለመውሰድ ችግር አልነበረባቸውም። በኬሻ ጠቅልለው አህያ ላይ ይጭኑትና፤ ከላዩ ከሰል ወይም እንጨት ይጭናሉ። ድኩላ ጭኖ ብዙ ኪሎሜትር ሳይነቃበት መሄድ የሚችል ኢትዮጵያዊ ታዲያ፣ ጥቂት መቶ በራሪ ወረቀቶችን ከአዲስ አበባ ደብረብርሃን፤ ወይም ወልቂጤ መውሰድ እያቅተውም።
9. መረጃን የማከፋፈል ስራን የሚወስዱ ሰዎች ለህዝባዊ አመጽ ቁልፍ ከመሆናቸው የተነሳ፣ የአምባገነናዊ አገዛዞች የደህንነት መዋቅር ዋና ኢላማዎች ናቸው። ስለዚህም በጥንቃቄ መመላለስ አለባቸው። ለምሳሌ፥ በራሪ ወረቀቶችን እያባዙ ማከፋፈሉን በአንድ ማእከላዊ ስፍራ ከመስራት ይልቅ፤ ለተለያዩ እና ለማይተዋወቁ አካላት ማከፋፈሉ ይቀላል።
10. እራስን መከላከል። አምባገነኖች ሲጠበቡ፤ ሰው ከቅጠል ለይተው አያዩም። አገርንም ከአንድ ብጣሽ ወረቀት አስበልጠው አያዩም። መጨፍጨፍ ያለባቸውን ይጨፈጭፋሉ፤ ማቃጠል ያለባቸውን ሁሉ ያቃጥላሉ። በአንድ አገር ለውጥ የማምጣት ተግባር፤ በተለይም አምባገነናዊ አገዛዝን የማስወገድ ስራ፤ መስዋእትነትን የሚያስከፍል ነው። ከቤትህ ስትወጣም ይህንን አውቀህ ነው። ይሁን እንጂ፥ እስከ ሞት የሚደርስ መስዋእትነት ለነጻነትህ እና ለአገርህ ለመክፈል ዝግጁ ብትሆንም፤ እሞታለሁ ብለህ ግን ከቤትህ አትውጣ። አላማህ ለመኖር፤ ድል ለማድረግ እና ነጻ አየር ለመተንፈስ ይሁን። ውድ የሆንክ የፈጣሪ ልጅ መሆንህን፤ አገርህም ከመኖርህ እንጂ ከመሞትህ እንደማታተርፍ አትርሳ። ስለዚህ እራስህን ከጥቃት መከላከልን ጠንቅቀህ አስበህበት ውጣ።
11. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፥ ባለፉት አምስት አመታት ሰልፈኞችን መቆጣጠር በሚችልበት መንገድ ላይ ከምእራባውያን መንግስታት ስልጠና አግኝቷል። በርካቶች፥ አገዛዙ ገና ከጅማሬው ግብጽ እና ቱኒዚያ እንዳደረጉት አስለቃሽ ጭስ መርጨት ሳይሆን፣ ጥይት መተኮስ እንደሚጀምር ይገምታሉ። ያ እንዳለ ሆኖ፥ ለይስሙላ ያህል፤ ለፈረንጆቹ፥ "ይኸው የሰጣችሁኝን ጋስ ተጠቅሜበታለሁ" ለማለት፤ ወይም ከተኩሱም አቀላቅሎ አስለቃሽ ጭስ የሚረጭ ከሆነ፤ በኮምጣጤ እና በሎሚ ጭማቂ የተነከሩ ሻሾችን ይዞ ከቤት መውጣት እና ጋሱ መረጨት ሲጀምር ያንን ወደ አይን ማቅረብ ይረዳል ይባላል። ለማንኛውም፥ አፍና አፍንጫ ለመሸፈን፤ እንዲሁም በወገን ላይ አደጋ ቢደርስ ቁስል መሸፈኛ እንዲሆን፤ በተቻለ መጠን ነጠላ እና ሻሽ ይዞ ከቤት በውጣት ይጠቅማል።
12. ምግብና ውሃ። የትግራዩ ገዢ ቡድን፥ ከዚህ ቀደም ከኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር ጋር ጦርነት በሚያካሄድበት ወቅት፤ ወደ ኦጋዴን የሚወስዱ መንገዶችን በመዝጋት ህዝቡን በረሃብ የመጨረስ "ስልት" ተብዬ ጭካኔ ተጠቅሞ ነበር። አምባገነናዊ አገዛዞች አልገዛ ያላቸውን ህዝብ በማስራብ ይታወቃሉ። አገዛዙ አሁንም ተቃውሞ ቢነሳበት፤ ይህንን ስልት ሊጠቀም ይችላል። ይሁን እንጂ፥ ይህ ኢትዮጵያውያንን የሚያሰጋ ጉዳይ አይደለም። በአገራችን፥ እንኳን በመንደሮች እና በትናንንሽ ከተሞች ይቅርና፤ በመዲናይቱ ውስጥ እንኳ፣ ብዙው ሰው ትንሽም ትሁን ጓሮ እና ግቢ አለው። ይህ ማለት ደግሞ፥ ቲማቲም፣ ካሮት፣ ጎመን፣ ድንች እና የመሳሰሉትን በቀላሉ እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ማብቀል ይችላል። እነዚህ አትክልት፤ ያለ እንጀራ በተለያየ መልክ ተዘጋጅተው ሊበሉ ይችላሉ። እንደ ስኳር እና የምግብ ዘይት የመሳሰሉትን ለተወሰነ ጊዜ ማጣት በሰውነት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት የለም። የመጠጥ ውሃ ችግርን ለመቀነስ፤ እያንዳንዱ መንደር በመተባበር ቢሪ/ወይም የውሃ ጉድጓድ መቆፈር ይችላል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ለስኬታማ ህዝባዊ አመጽ ልንጠቀምባቸው የሚገቡን ዘዴዎች

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

የጉድጓድ ዉሃ ብዙውን ጊዜ ለመጠጥነት ንጹህ ቢሆንም፤ በቀላሉ ማጽዳት፣ ወይም አፍልቶ እና አቀዝቅዞ መጠጣት ይችላል። እንግዲህ እነዚህ ከሁሉ አስቀድሞ ሊደረጉ የሚገባ ዝግጅቶች ናቸው።

13. የአላማ ጥራት እና ጽናት። የምናምጽበትን ምክንያት ጠንቅቀን ማወቅ ከብዙ አደጋ ይጠብቀናል። በራሳችን እና በአገራችን ላይ ጊዜያዊም ሆኔ ዘላቂን ጉዳት ከማድረስ ያተርፈናል። ሰሞኑን በግብጽ፥ ተስፋ የቆረጠው መንግስት የደህንነት ሰራተኞቹ እና ከእስር የተለቀቁ ወንጀለኞች የህዝብ እና የአገር ንብረት እንዲዘርፉ መንገድ ላይ ለቋቸዋል። የዚህ ዘረፋ ሰለባ ከሆኑት ተቋማት እንዱም ከአለም ታሪካዊ ቅርሶች ውስጥ ሶስት አራተኛውን ይዟል የሚባለው የአገሪቱ ሙዚየም ነው። ይህ ሲሆን፤ ሰልፈኞቹ እጅ ለእጅ ተያይዘው በሙዚየሙ ፊት በመቆም ከዘራፊዎቹ ጋር ትልቅ ተጋድሎን በማድረግ የአገራቸውን ሃብት ተከላክለዋል። ይህ ሲሆን፥ ሰልፈኞቹ ዞር ብለው ከዘረፋው በመቀላቀል እራሳቸውን ሊጠቅሙ ይችሉ ነበር። ነገር ግን የወጡበት አላማ ያ እንዳልሆነ፤ ከምንም በላይ ደግሞ የአገርን ሃብት እና ቅርስ መጠበቅ የያንዳንዱ ዜጋ ሃላፊነት እንደሆነ ስለተረዱ በርትተው ቆሙ። የትግራዩ ገዢ ቡድን ባለስልጣናት፥ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቅርሶች ከአገር እያስወጡ እንደሚሸጡ ከዚህ ቀደም ተወርቷል። በቅርቡ በኢትዮጵያ ህዝባዊ አመጽ ቢከሰት፣ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው የተለያዩ የህዝብ እና የመንግስት ተቋማትን ለማስዘረፍ እንደሚሞክሩ እና በሰልፈኞች ላይ እንደሚያላክኩ ይገመታል። ዝርፊያ በሌለበት ዝርፊያ ተፈጽሟል ብለው እንደሚከሱ ከምርጫ 97 ልምዳችን እናውቃለን። ታዲያ በእንዲህ አይነቱ ወቅት የአገርን ሃብት ሊጠብቅ የሚችለው ዜጋው ብቻ ነውና፤ ለዚህ እንዘጋጅ።

14. የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፥ ከዚህ ቀደም ጭንቀት ውስጥ ሲገባ የዘር እና የሃይማኖት ግጭት እንደሚያነሳሳ ከልምዳችን እናውቃለን። ወደፊትም ቢሆን አጣብቂኝ ውስጥ ሲገባ ያንን ለመቀስቀስ ተዘጋጅቶ እና፤ ያንን ስራ የሚሰሩለትን ሰዎች በዙሪያው ኮልኩሎ እንደሚቀመጥ ጠንቅቀን እናውቃለን። ባለፈው ሳምንት በግብጽ የሆነው ክስተት ከዚህ አኳያ ትልቅ ትምህርት ሊሆነን ይችላል። ሙስሊሞች ወደ ጁማአ ጸሎት ሲገቡ፤ ክርስቲያን ወንድሞቻቸው ውጪ ቆመው ጸሎተኞቹን እና መስጊዶችን እንደሚጠብቁ ቃል ገቡ። እኛም በኢትዮጵያችን እንደዚህ ያለ ፍቅርን እና መተሳሰብን ልናሳይ ይገባናል። ከሁሉ አስቀድመን፤ ባህላችን እና ሃይማኖቶቻችን ስለ ጉርብትና የሚያስተምሩንን አንርሳ። መለስ ዜናዊ የሲቪል ልብስ የለበሱ ቅጥረኞቹን አሰማርቶ በዚህና በዚያ ዘውጌ ማህበረሰብ ላይ፤ በዚህና በዚያ ሃይማኖት አባላይ ላይ ተነሳ እያለ በጆሮህ ቢያንሾካሹክ፤ ጥላቻን የሚያውጀ በራሪ ወረቀቶች በአገዛዙ ሰዎች ተዘጋጅተው ቢበተኑ፤ አንዱንም አትስማ። አንተ የወጣኸው ነጻነትን እና የተሻለ ኑሮን ፍለጋ እንጂ ወገኖችህን ልታጠቃ አይደለም። ስለዚህም፥ በአቋምህ ጽና።

15. ሰልፈኞች፥ የህዝብ ንብረት እነሱን ለማፈኑ ስራ ጥቅም ላይ ሲውል ሲያዩ፤ ያንን ንብረት እንደ ጠላት ንብረት ያያሉ። ለምሳሌ በግብጽ በርካታ የፖሊስ መኪናዎች ተቃጥለዋል። ህዝቡ ይህን በማድረጉ ወንጀል አልፈጸመም፤ እራሱን የመከላከል መብት ስላለው። ይሁን እንጂ፥ ይህ አምባገነኖች የሚጠቀሙበት ተሽከርካሪ ወይም ህንጻ፤ ዞሮ ዞሮ የኛው ንብረት ነው። ሲቃጠል የሚከፍለው ህዝብ ነው እንጂ አምባገነኑ አይደለም። ታዲያ እንዴት አድርገን እራሳችንን እንከላከል? ላሰበበት ሁልጊዜም ቢሆን የተሻለ አማራጭ አይታጣም። ለምሳሌ፥ ሰሞኑን አንዳንድ ብልጥ የግብጽ ወጣቶች፤ የፖሊስ ተሽከርካሪዎችን በማቃጠል ፈንታ፤ ባትሪዎቻቸውን በማስወገድ እና ከፖሊሶቹ አይን በመሰወር መኪናዎቹ እንዳይንቀሳቀሱ አድርገዋል። ይህ አንድ ዘዴ ነው።

16. ድፍረት። እንግዲህ አምባገነናዊ አገዛዞችን ለመገልበጥ፤ በመጀመሪያ ፍርሃትን ማሸነፍ ይገባል። በአመጽ ስራ የሚሳተፉ ሰዎች፤ ብዙ ጊዜ መጀመሪያ ላይ ፍርሃት እንደሚሰማቸው ይናገራሉ። ነገር ግን የመጀመሪያዋን እርምጃ ከወሰዱ በኋላ፤ ስጋታቸው እየሟሸሸ ይሄድና ጨርሶ ይጠፋል። ስለዚህ፥ ጀግና ሁሉ ከፍጥረቱ ጀምሮ ደፋር ነበር የሚል አመለካከት ከያዝን ተሳስተናል። ድፍረት የሚገኘው በሂደት ነው። እናም የመጀመሪያዋ እርምጃ ወሳኝ ነች።

እንግዲህ፥ እነዚህ የሃሳብ ስብስቦች ያቀረብነው፤ ለችግር ሁሉ መፍትሄ በገዛ እጃችን እንዳለና፤ ለሰው አእምሮ የማሰብ ችሎታ ማቆሚያ እንደሌለው ለማሳሰብ ያህል ነው። የኢትዮጵያ ወጣቶች ከቱኒዚያ እና ከግብጽ ወጣቶች በምንም በኩል አያንሱም። ማለቂያ የሌላቸው ግሩም ሃሳቦች ማፍለቅ እንደሚችሉ አንጠራጠርም። ከምንም በላይ ልናስታውሳቸው የምንወደውም ይህንኑ ነው። እንደሚችሉ!

## የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በኢትዮጵያ ያወጀው የዋጋ ተመን የዘር ትስስር ያላቸውን ነጋዴዎች እንደማይነካ ተነገረ

መለስ ዜናዊ የሰሜን አፍሪካው ህዝባዊ አመጽ እሱም ጋር እንዳይደርስ በመስጋት በችኮላ ያወጀው የዋጋ ተመን አንዳንድ ነጋዴዎችን እንደማይመለከት ከአዲስ አበባ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

የግንቦት 7 ሪፖርተር ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው ሪፖርት፥ ሌሎች ነጋዴዎች የዋጋ ተመኑን በስራ ላይ አላዋላችሁም በሚል እየታሰሩ፤ ከአገዛዙ ባለስልጣናት ጋር የዘር ትስስር ያላቸው ነጋዴዎች ግን ሸቀጣሸቀጦቻቸውን ባሻቸው ዋጋ እንዲሸጡ ተፈቅዶላቸዋል። ከሁለት ሳምንታት በፊት ተመኑ በታወጀ ማግስት ከ100 በላይ ነጋዴዎች አዋጁን በስራ አልተረጎማችሁም በሚል መታሰራቸው ይታወሳል።

ለምሳሌ ያህል፥ ሃሊውድ የተባለ እና በ22 መገናኛ አካባቢ የሚገኝ መጠጥ ቤት፤ በቢራ ላይ የተጣለውን ተመን ወደ ጎን በመተው ለአንድ ቢራ የቀድሞውን 15 ብር እንደሚያስከፍል ዘጋቢያችን የላካቸው ተጠቃሚዎች መስክረዋል። ሌሎችም በርካታ ከአገዛዙ ጋር ትስስር ያላቸው ሰዎች መጠጥ ቤቶች እና አገልግሎት ሰጪዎች የዋጋ ተመኑን እንደማይከተሉ ዘገባው አመልክቷል።

የወያኔ አገዛዝ በተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ጨቋኝ እርምጃዎችን በወሰደ ቁጥር፤ ለራሱ እና ቅርብ ለሆኑት ነጋዴዎች ግን የንግድ እድል የመፍጠር አሰራር እንዳለው ይታወቃል። ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ በአስር ሺሆች የሚቆጠሩ ንጹሃን በግፍ ሲታሰሩ፤ የወያኔ ባለስልጣናት ንብረት የሆነው ትራንስ ኢትዮጵያ እስረኞችን የማጓጓዝ ኮንትራት ተሰጦት ከፍተኛ መጠን ያለው ክፍያ ከህዝብ ካዝና እንደተከፈለው ይታወቃል።

## የቱንዚያው ህዝባዊ ማእበል ተከትሎ ህውሀትና . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እናቶች ስብስቦ ወጣት ልጆቻቸው በጸረ መንግሥት ተቃውሞ እንዳይሳተፉ ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር ከመስጠት ጀምሮ "አገር የከዱ የኢትዮጵያ ጠላቶች ሃገሪቱዋ እንድትጠፋ ተንኮል እየሸረቡ ነው፣ መንግሥታችን እያከናወነ ያለውን የልማት ስራ ሊያደናቅፉ እና ህዝቡን ለ ዕልቂት እያነሳሱ ነው ፤ ኢሳት የተባለው ተለቪዝን የሚዲያ ጦሪነት ከፍቶብናልና ሰለባ እንዳትሆኑ ወዘተ " የሚል ፕሮፓጋንዳ በህዝቡ ውስጥ እንዲነገር ትእዛዝ ማስተላለፋቸውን ለማወቅ ተችሎአል። ከዚህም በተጨማሪ የወያኔው አገዛዝ ወታደሮችና ፖሊሶች በተጠንቀቅ እንዲጠብቁ፣ አድማ በታኝ ፖሊሶች ተጨማሪ ስልጠና እንዲወስዱና የአድማ መበተኛ ተሽከርካሪዎች ውሃ እየሞሉ በተጠንቀቅ ሆነው ት ዕዛዝ እንዲጠባበቁ መመሪያ መተላለፉ ታውቆአል ። በተያያዘ ዜና በዘረኛ የወያኔ መዋቅር ተጠቃሚ ከሆኑት የትግራይ ተወላጆች አንዷ የሆነቿው የቀድሞው የቪ ኦ ኤ ጋዘጠኛ ሚሚ ስብሃት የተባለች ሴት ንብረት የሆነው ዛኑ በመባል የሚታወቀው ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ "የኢትዮጵያ ጠላቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ግጭት እንዲከሰትና በሃገሪቱም አለመረጋጋት እንዲፈጠር እየሰሩ ናቸውና ተጠንቀቁ" የሚል መለክት በየቀኑ እያስተላለፈ መሆኑ ታውቁአል። ላለፉት 20 አመታት ማን ምን እንደሆነና ለምን ወያኔ ዕድሜ ለማራዘም እንደሚተጋ የተረዳው የኢትዮጵያ ህዝብ ለወያኔ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ቁብ ሳይሰጥ ሁኔታውን በቅርበት እየተከታተለ እንደሆነ ከህዝብ የተገኘው አስተያየት ያመለክታል። በተለይ ወጣቱ ትውልድ "እን ነሳ" የሚል የስልክ መል ዕክት ኤ ስ ኤም ኤስ እየተለዋወጠ እንደሆነ ሪፖርተራችን አክሎ ገልጾአል።

ይህ በዚህ እንዳለ በቱኒዚያ ህዝባዊ አመጽ ከተቀሰቀሰ ወዲህ በሰሜን አፍሪቃ በርካታ ሃገራት ተመሳሳይ ንቅናቄዎች እየተደረጉ ከመሆኑ አልፎ የመንግሥት ለውጥ ጥያቄው ወደ መካከለኛውና ምስራቅ አፍሪቃም በፍጥነት በመገስገስ ላይ መሆኑን ሮይተርስ የዜና ወኪልን ጨምሮ በርካታ የዜና አውታሮች በመዘገብ ላይ ናቸው። ይህ የተቀጣጠለ የህዝብ አመጽ ባለፈው ማክሰኞ በሱዳንም በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አማካኝነት የተጀመረ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በሰልፉ በአስር ሺሆች የሚቆጠሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መሳተፋቸውም ታውቁአል:: በሱዳን የተካሄደውን የተቃውሞ ሰልፍ ለመበተን እጂግ በርካታ ፖሊሶች የተሰማሩ ሲሆን ፖሊሶቹ ከሰልፈኞች ጋር መጋጨታቸውንና በርካታ ተማሪዎችን መታሰራቸው ታውቁአል፡፡ ሮይተርስም ባወጣው ዜናው በፖሊሶች የተደበደበ አንድ ሱዳናዊ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ህይወቱ ማለፉ ታውቁአል::

ከዚሁ የምስራቅ አፍሪቃ ክልል ሳንወጣ የዩጋንዳ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችም የሃገሪቱ መንግስት የቀረቡለትን ህዝባዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ርምጃ የማይወስድ ከሆኑ በቱኒዚያና በግብጽ የታየው አይነት ህዝባዊ ተቃውሞ እንደሚገጥመው ከወዲሁ እየገለጹ ነው:: እንደ ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘገባ ላለፉት ሃያ አምስት አመታት በስልጣን ላይ የቆዩት ሙሶቬኒ የህዝብ ጥያቄን መመለስ ከተሳናቸው የሚጠብቃቸው ተቃውሞ ቀላል እንደማይሆን የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎቹ አስጠንቅቀዋል::

እንደ ሌሎች የሰሜን አፍሪቃ ሃገራት ሁሉ በመካከለኛው እንዲሁም በምስራቅ የአፍሪቃ ሃገራት ለህዝብ አመጽ መንሴ እነደሆኑ እየተገለጹ ያሉት በየአገሮቹ እየናረ የመጣው የምግብ ዋጋና የባለሥልጣናቱ በሙስና መዘፈቅ መሆኑ ታውቁአል።

በሌላም በኩል ተመሳሳይ የሆነ የህዝብ አመጽ በጋቦን መከሰቱን ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቡአል:: በጋቦን በተቀሰቅሰ ህዝባዊ አመጽ ሰልፈኞች ከፖሊስ ጋር መጋጨታቸው ታውቁአል :: የመንግስት ተቃዋሚ በሆኑ ከአምስት ሺህ በላይ የሆኑ ተቃዋሚዎች በተሳተፉበት ህዝባዊ አመጽ በተነሳው ግጭት ከሃያ በላይ የሚሆኑ ዜጎች ላይ ጉዳት መድረሱን ሮይተርስ የዜና ወኪል ዘግቡአል::

ይህ በሰሜን አፍሪካ እና በመካከለኛው ምሥራቅ እንደ ሰደድ እሳት እየተያያዘ ያለው ሕዝባዊ አመፅ ቀጥሎ ወዴት ያመራል የሚለው ጥያቄ በስፋት እየተነሳ ሲሆን በተለይም ኢትዮጵያዊያን በሃገሪቱ እየታየ ካለው እጂግ የከፋና ውስብስብ ችግር አንጻር ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ህዝባዊ አመጽ ሊነሳ እንደሚችል ምንም ጥርጣሬ እንደሌላቸው እየገለጹ ነው::

የአፍሪካ ህብረትን በንግግር የከፈቱት የፈረንሳዩ ሜሪ ሳርኮዚ አምባገነን የአፍርካ መሪዎች በየአገሮቻቸው ዲሞክራሲያዊ የመንግሥት ለውጥ ካላካሄዱ በቱኒዚያ የተነሳው ህዝባዊ አመጽ በየአገሮቻቸው እንደሚፈነዳና እንደሚበላቸው በግልጽ ተናግረዋል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



ውድ አንባቢዎቻችን

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org